ቁጥር/Ref.No: ኢሲማድም/ሲ7/244/15
ቀን/Date: መስከረም 06/2015ዓ.ም

# ጋዜጣዊ መግለጫ

**የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት  የሰላም ጥሪውን በድጋሚ እያቀረበ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ዳግም ባገረሸው ጦርነት ሳቢያ ጉዳት ላይ ለወደቁ ወገኖች አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ በአፋጣኝ እዲደረግ አበክሮ ይጠይቃል።**

**መስከረም 6 ቀን 2015 ዓ.ም አዲስ አበባ፡-** የኢትየጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሃገራችን የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ለማስተባበርና ለመወከል  በአዋጅ የተቋቋመ ድርጅት መሆኑ ይታወቃል። ምክር ቤቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና በብቃት እንዲያከናውኑ ሁለንተናዊ ድጋፍና እገዛ ከመስጠት ጀምሮ ተቋማቱ ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት የሚያስችላቸው የሲቪክ ምህዳር ምቹ ሆኖ እንዲቀጥል ይሰራል። በተጨማሪም ምክር ቤቱ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የህዝብን ጥቅም በማስቀደም የሲቪክ ምህዳሩን በሃላፊነት መጠቀማቸውን እንዲቀጥሉ ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ምክር ቤቱ የዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ግቦች እውን ማድረግ የሚቻለው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በሰላምና ልማት ሂደት እንዲሁም ሰብዓዊ ድጋፍን ጨምሮ በሚደረጉ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴዎች መሆኑን አጥብቆ ያምናል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሃገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መግለጫ ማወጣት ብሎም የሰላም ጥሪ ማቅረብ እንደሚችሉ፤ ይህም ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች  መሰረታዊ ባህሪያት አንጻር የሚጠበቅ መሆኑን ምክር ቤቱ ያምናል።

በዚህ አሳሳቢ ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ዳግም በተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያት ለጉዳት የተጋለጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ለመደገፍ  አስቸኳይ የሰብዓዊ ዕርዳታ ተደራሽ በማድረግ ስራ ላይ እንዲረባረቡ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት  ይጠይቃል።

ለዚህም ምክር ቤቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በማስተባበርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት በመስራት ለዘላቂ ሰላም ግንባታ እና ለሰብአዊ ድጋፍ የሚደረገውን ጥረት ሁሉ መደገፉን አጠናክሮ ለመቀጠል ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ ይገልጻል።

በተጨማሪም የመገናኛ ብዙሃን የጋዜጠኝነት ስነ ምግባርን በጠበቀ መልኩ ገንቢ እና ኃላፊነት የተሞላበት ዘገባ ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ ምክር ቤቱ ጥሪውን ያቀርባል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ኢትዮጵያውያን አሮጌውን አመት ሸኝተን አዲሱን አመት በተቀበልንበት በዚህ ወቅት በሰላም፣ በመረጋጋት እና በሰብአዊ መብት ጉዳዮች ላይ በጋራ በመስራት ሃገራችን ከተደቀነባት አደጋዎች የምትላቀቅበት መልካም ዘመን እንዲሆን እንመኛለን።

***<u>ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት</u>***

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን በኢፌዲሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግበው ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ3700 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።*